## በውጭ ሀገር ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የቤት መግዣ ከወለድ ነፃ የፋይናንስ አገልግሎት

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በውጭ ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የቤት መሥሪያ ወይም መግዣ የፋይናንስ አገልግሎት አቅርቧል።

ይህ አገልግሎት ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ከወለድ ነፃ በሆነ አገልግሎት ባንኩ የሚሰጠውን የፋይናንስ አገልግሎት እንዲጠቀሙ የሚያስችል ነው።

### የቤት መግዣ ፋይናንስ አገልግሎት መገለጫዎች

- የፋይናንስ አገልግሎቱ ለመኖሪያ ቤት መግዣ ብቻ የሚውል ነው፤
- ባንኩ አገልግሎቱን የሚያቀርበው በሸርዓ መርህ የሙራባሃ አሰራርን ተከትሎ ይሆናል፤
- ደንበኛው የሽያጩን ክፍያ ለባንኩ ከፍሎ የሚያጠናቅቀው ከ20 ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ነው፤
- ደንበኛው የሚከፍለው ቅድመ-ክፍያ የሚገዛውን ቤት ዋጋ/ግምት ቢያንስ 20 በመቶ ይሆናል፤
- ባንኩ ላቀረበው የፋይናንስ አገልግሎት የሚያስከፍለውን የትርፍ መጠን በቤቱ ዋጋ፣ ክፍያ የማጠናቀቂያ ጊዜ ርዝማኔ፣ እና ደንበኛው በመረጠው የፋይናንስ አማራጭ የሚወሰን ይሆናል።

### የቤት መግዣ ወዲዓ ቁጠባ ሂሳብ የት መክፈት ይቻላል?

- አመልካቹ ከ1,400 በላይ በሚሆኑት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከወለድ ነፃ የባንክ አገልግሎት በሚሰጡ ቅርንጫፎች ወይም በሚኖርበት ሀገር በሚገኝ የኢትዮጵያ ኤምባሲ በአካል በመቅረብ ወይም በሕጋዊ ወኪሉ አማካይነት የ"ወዲዓ ቁጠባ ሂሳብ" በመክፈት ለመጀመሪያ ክፍያ የሚሆነውን ገንዘብ መቆጠብ ይችላል።
- አመልካቹ አዲስ አበባ ከሆነ የአገልግሎት ጥያቄውን ለባንኩ ከወለድ ነፃ የባንክ አገልግሎት ክፍል፤ ከአዲስ አበባ ውጭ ከሆነ ደግሞ ለሚመለከተው ዲስትሪክት ቢሮ ወይም የቁጠባ ሂሳቡን ለከፈተው ቅርንጫፍ ማቅረብ ይችላል።

### ለአገልግሎቱ ብቁ የሚያደርጉ መስፈርቶች

- ማንኛውም እድሜው 18 ዓመት እና ከዛ በላይ የሆነ ዳያስፖራ፣
- ዳያስፖራው አገልግሎቱን ሲጠይቅ የሚከተሉትን ሰነዶች ማሟላት ይኖርበታል፣
  - አመልካቹ ኢትዮጵያዊ ከሆነ የታደሰ ፓስፖርት፣ የመኖሪያ እና/ወይም የሥራ ፈቃድ፤
  - አመልካቹ ትውልደ ኢትዮጵያዊ የሆነ የውጭ ዜጋ ከሆነ የታደሰ ፓስፖርትና የትውልደ ኢትዮጵያውያን መታወቂያ (ቢጫ ካርድ)፤
  - ሁለት የቅርብ ጊዜ የፓስፖርት መጠን ያላቸው ፎቶግራፎች፣
  - የጋብቻ ምስክር ወረቀት፣ ወይም ያላገባ ከሆነ ይህንኑ የሚያረጋግጥ ሠነድ፣
  - የአገልግሎቱ ጥያቄ የቀረበው በወኪል አማካይነት ከሆነ የተወካዩ የታደሰ መታወቂያ ኮፒ፣ሁለት ፓስፖርት መጠን ያላቸው የቅርብ ጊዜ ፎቶግራፎች እና የውክልና ማስረጃ፤
  - እንደ አስፈላጊነቱ ጠቅላላ ዓመታዊ የደመወዝ መጠን እና የተጣራ ገቢን የሚገልጽ ከቀጣሪው የተሰጠ የቅጥር ደብዳቤ፣
  - እንደ አግባብነቱ የቅጥር ውል ኮፒ፤
  - ከውጪ ሀገር ባንክ ቢያንስ የአንድ ዓመት የሂሳብ መግለጫ፣
  - አመልካቹ በንግድ ሥራ የሚተዳደር ከሆነ፣
    - የሦስት ተከታታይ ዓመታት የሂሳብ ዝርዝር መግለጫ፣
    - የታደሰ የንግድ ፈቃድ እና የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት (እንደአግባብነቱ)፣ እና
    - የግብር ክፍያ ምስክር ወረቀት ማቅረብ ይኖርበታል።
- አመልካቹ የመኖሪያ ቤት መግዣውን ቢያንስ 20 ከመቶ በውጭ ምንዛሪ መክፈል ወይም መቆጠብ አለበት፤
- የሽያጭ ሂደቱን ካጠናቀቀ በኋላ ደንበኛው የሚጠበቅበትን ወርሃዊ ክፍያ በባንኩ ተቀባይነት ባላቸው የውጭ ሀገራት ገንዘቦች (የአሜሪካን ዶላር፣ የእንግሊዝ ፓውንድ ወይም ዩሮ) መፈፀም አለበት።

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ
**Commercial Bank of Ethiopia**



## Interest Free Banking (IFB) Diaspora Mortgage Financing